05

ፍኖ ዓመት ቁጥር 10
6th Year No 10

ባህር ዳር መጋቢት 18 ቀን/1993
Bahir Dar 27th March/2001

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

ዝክረ ህግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 3.33	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	ፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.Box

ማውጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 56/1993 ዓ.ም የብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ገፅ 7	Proclamation No 56/2001/ A Proclamation Issued To Establish The Mass Media Agency Page 7

አዋጅ ቁጥር 56/1993 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመገናኛ ብዙሃን መገናኛ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የክልላችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ እየጎለበተና እያደገ በመምጣቱ ምክንያት የክልላችንን የመንግሥት ብዙሃን መገናኛዎች የሥራ ስፋት፣ ጥልቀትና የአቅርቦት ጥራት ይበልጥ በማጠናከር ለክልሉ ልማት ተጨውን የአጋዥነት ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በመንግሥት ባለቤትነት ሥር ባሉ የክልላችን የብዙሃን መገናኛ ተቋማት የተለያዩ ሃሳቦችና አመለካከቶች በዙሪያቸው ውስጥ በህገ መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ/ብዙሃን መገናኛዎቹ ይበልጥ የተጠናከረ የተቋምና የአሠራር ነፃነት እንዲኖም የህግ ጥበቃ እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፣

የክልላችን ብዙሃን መገናኛ ራሱን አስችሎ በአዲስ መልክ በማደራጀት የሥራ ዕድገቱና ቅልጥፍናው በተሻለ መንገድ እንዲመራና እንዲራመድ ብሎም በክልሉምንባር-

Proclamation No 56/2001/
A Proclamation Issued To Establish The Mass Media Agency Of The Amhara National Regional State

WHERE AS, the economic, political and social activities of our region are so growing in a such away that it has become necessary to widen and strengthen the capacity and quality of the regional state mass media in order that they could play a facilitating role in the over all development of the region;

WHERE AS, it is necessary to provide for the institutional & operational autonomy as well as legal protection to the government owned regional mass media with a view to ensuring the free expression of different opinions and views among the population in accordance with the provisions of the constitution;

WHERE AS, It has become necessary to re-organize the regional mass media in a new and autonomous way, provide for the better management of its growing tasks and enhance its

ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና በዲሞክራሲ ግንባታ ረገድ ተጫዉን ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ዓለማዊና አገራዊ ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ፍላጎት እያደገ መምጣቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት ክልላዊ የብዙሃን መገናኛዎች የሕብረተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች በቅርበትና በሰፋት በመዘገብ ሊጫወቱ የሚችሉትን ሚና በመረዳት የክልላችን ብዙሃን መገናኛዎችም አሁን ካለብት በተሻለ መልኩ ተዋዳሪው በአገሪቱ ካሉ ሌሎች የብዙሃን መገናኛዎች ጋር በገበያ ተወዳዳሪ ሆነው ኃላፊነታቸውን በተሻለ ደረጃ እንዲወጡ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 56/1993 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አዝብብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. " ቦርድ " ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/1/ እና አንቀጽ 8/1/ መሠረት የተቋቋመው የብዙሃን መገናኛ ድርጅት ሥራ አመራር ቦርድ ነው።
2. "የብዙሃንመገናኛ" ማለት በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በጋዜጦችና በመጽሔቶች አማካኝነት መረጃ /አንፎርሜሽን/ የማሰባሰብና የማሠራጨት ሥራዎችን የሚያከናውኑ፣ የዜና እና የፕሮግራም ሥራዎችንና መጣጥፎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር በልዩ ልዩ ዘዴዎች ለሕዝብ የሚያሠራጩ ወይም እነዚህኑ በቀጥታ ለሚያስተላልፉ ሌሎች ተቋማት የሚያከፋፍሉ ተቋማት ናቸው።
3. "ጋዜጠኛ" ማለት በአዘጋጅነት፣ በአርታኢነት፣በዘጋቢነት፣ በኮርቱን አዘጋጅነት በግራፊክስ ባለሙያነት፣በፎቶ ግራፍ አንሺነት፣ በተንቀሳቃሽ ፊልም አንሺነት፣ ወይም በቴክኒሺያንነት ዜና እና መረጃዎችን ሰመሰብሰብ በመቀበልና በማሠራጨት ሙያ የተሠማራ ማናቸውም ሰው ነው።
4. " ሰው " ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. ስለ መቋቋም

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የብዙሃን መገናኛ ድርጅት ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ፣ ህጋዊ ሰውነት ያለውና ራሱን የቻለ መንግሥታዊ ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የክልሉ መንግሥት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8/2/ መሠረት ለሚሰየመው የብዙሃን መገናኛ ድርጅት ሥራ

efficiency as well as to enable it contribute in the socio-economic activities and growth of democracy in the region;

WHERE AS, there has been an increase in the need for speedy global and national information exchange, and there currently appears to a general understanding that the regional mass media can play a significant role in reporting the day to day activities of the society; And where as such an opportunity makes it essential to organize the regional mass media in a better way so that they could compete in the market with other media in the country and discharge their responsibilities efficiently;

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National regional state, in accordance with The powers vested in it, under article 49 sub-article 3(1) of the constitution, hereby proclaims as follows.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This proclamation may be cited as '' The Amhara National Regional State Mass Media Agency Establishment Proclamation No 56/2001."

2. Definitions

Unless, the context requires otherwise in this proclamation:

1. '' Board'' Means the managing board of the mass media agency established pursuant to arts 6/1/ and 8/1/ of this proclamation.
2. '' Mass media'' means institutions which are engaged in collecting and distributing information through radio, television, newspapers and magazines as well as collecting, organizing and distributing news and programmers to the people through different means or distribute to other institutions which transmit them directly.
3. ''Journalist '' means any person who may be engaged as an editor, chief editor, producer, reporter cartoonist, graphic artist, photographer, cameraman or technician exercising such professional activity as seeking, receiving or dissemination of news and information.
4. '' Person'' means any natural or juridical person,

3. Establishment

1. The Amhara National Regional State mass media Agency, thereinafter referred to as '' The Agency'' is hereby established as an autonomous governmental organization having legal personality.
2. The Agency having been established for unspecified period of time, shall be accountable to the executive committee of the Amhara National Regional state and the managing board of the Agency assigned by the Regional state in accordance with

አመራር ቦርድ ይሆናል።

4. የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት

1. የድርጅቱ ዋና መቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል።
2. ድርጅቱ አንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ ቅርንጫፎችና ወኪል ጽህፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5. ዓላማዎች

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. በፌዴራልና በክልሉ ህገ-ጋት መንግሥታት፣ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ፖሊሲዎች፣ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሃሳብን በነፃ የመገለጽ ነፃነትን ማበረታታት፣
2. በክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አጋዥ ሚና መጫወትና በህብረተሰቡ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ባህልን ማጎልበት

ክፍል ሁለት
ስለ ድርጅቱ አወቃቀርና ሥልጣን

6. ድርጅታዊ አቋም

ድርጅቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል

1. የሥራ አመራር ቦርድ
2. ሥራ አስኪያጅ
3. ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች

7. የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ለክልሉ ህዝብ ጠቃሚነታ ያላቸውን አስፈላጊ ዜናና ዜና ነክ መረጃዎች በፕሬስ ውጤቶች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ያሠራጫል፣ ለዚህም እንዲረዳው እንደአስፈላጊነቱ መደበኛ የጋዜጣና የመጽሔት ሀትመቶች አንዲሁም የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እንዲኖሩት ያደርጋል።
2. የክልሉ መንግሥት ቃለ አቀባይ በመሆን ይሠራል።
3. የመንግሥትን ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃል።
4. የክልሉ ህዝብ ስለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለውን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚረዱ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ያቀርባል።
5. ነፃ የህዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፣ የሚመለከታቸውን በመጠየቅ ያጣራል፣ ውጤቱንም መልሶ ለሕዝብ ይገልጻል።
6. የህዝቡን ጠቅላላ እውቀት የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጎቱን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ጽሁፎችንና የሬዲዮም ሆነ የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን እየሠራ በተለያዩ ዘዴዎች ያሠራጫል።
7. ወቅታዊነት ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ተከታትሎ ይዘግባል።
8. የፎቶ ግራፍ፣ የምስል ዶክመንቴሽን፣ የህትመትና የማስታወቂያ አገልግሎችን ይሠጣል።
9. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የህትመት አገልግሎችንና የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ማቀናበሪያና የሥርጭት ማስተላለፊያም ሆነ ማሽንገሪያ አንዲሁም ለተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውሉ ሌሎች ተጭማሪዎችን እና መሳሪያዎችን በተገቢው ሥፍራ ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል።

article 8(2) of this proclamation.

4. **Head Office Of The Agency**

1. The Agency shall have its head office in Bahir Dar.
2. The Agency may, when never necessary, have branches and offices of representation in and out side the region.

5. **Objectives**

The Agency shall have the following objectives;

1. Encourage free expression of ideas in accordance with the federal and regional constitutions, other relevant governmental policies, laws, regulations and directives;
2. Playing a facilitating role in the economic, political and social activities of the region and promoting democratic culture through out the society

PART TWO
Organization And Powers Of The Agency

6. **Organizational structure**

The Agency shall have the following organs:

1. Board of management
2. Manager
3. Such other divisions as may be necessary

7. **Powers and duties of the agency**

The agency shall have the following powers and duties pursuant to this proclamation:

1. Broadcasts news and related information of current importance to the people of the region through press products, radio and television stations; and to accomplish same possession of regular news paper and magazine publications as well as radio and television programmers;
2. Works in the capacity of a spokesperson for the regional government;
3. Publicizes governmental policies, lows, regulations and directives;
4. Produces and presents programmers that help the people of the region develop proper awareness of the essence and use of human and democratic rights;
5. Receives and accommodates free public opinions and concerns; investigates by making inquiries visavis is those related with same and publicizes the results thereof;
6. Produces and transmits to the public educational, re-creational publications as well as radio and television programmers by using various means and methods;
7. Follows up and reports on the current economic, political and social affairs;
8. Delivers photography, image documentation, publication and advertisement services;
9. Establishes, organizes and administers, printing services as well as radio and television programmers; processing, transmitter and relay stations as well as other facilities and devices destined for similar services, as may be necessary for its operations;
10. Collects reasonable charges for the service it provides;

10. ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፣ እንደአስፈላጊነቱም በከፊል ወይም በሙሉ ከክፍያ ነፃ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።
11. የፕሬስ፣የራዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት በክልሉ ውስጥ የሚስፋፋበትንና በተሰማሚ ቴክኖሎጂ እየተጠናከረ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ እያጠና ለክልሉ መንግሥት ሃሳብ ያቀርባል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ይውላል።
12. በአገሪቱ ሕግ መሠረት በሀገር ውስጥና በውጭ ካሉ ተመሣሣይ ድርጅቶችጋር የዜና ዘገባና መረጃዎችን ለመለዋወጥም ሆነ የሥልጠና እና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችሉትን የሥራ ግንኙነቶች ይመሠረታል።
13. በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙና የማቴሪያልም ሆነ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኝነቱ ካላቸው ድርጅቶች በክልሉና በአገሪቱ ፖሊሲዎችና ህጎች መሠረት ድጋፍ ይሰባሰባል።
14. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሣል፣ይከሰሳል።
15. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሀጋፐያን ተግባራትን ያከናውናል።

ክፍል ሦስት
ስለ ድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድና ስለ ሥራአስኪያጁ

8. ስለ ቦርዱ አወቃቀርና ተጠሪነት

1. ድርጅቱ ከሰባት በማያንሱ ነገር ግን ከዘጠኝ በማይበልጡ አባላት በሚዋቀር የሥራ አመራር ቦርድ ይመራል።
2. የቦርዱ አባላት አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላትና የሕብረተሰብ ክፍሎች በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተመርጠ ይሰየማሉ።
3. የቦርዳ ተጠሪነት ለክልሉ መንግሥት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል
4. የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በክልሉ መንግሥት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሰየማል።

5.የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል።
6. ቦርዱ ስብሰባውን በሚያካሂድበት ወቅት ድምፅ የሌለው ሪዳት የቃለ ጉባዔ ያዥ ለሥራው ቅርበት ካለው አካል ሊያስመድብ ይችላል

9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚኮተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1.ድርጅቱ የብዙሃን መገናኛዎችን የሚመለከቱ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ማድረጉን ያረጋግጣል።
2. በሕዝብ ሊታወቁ የሚገባቸውን የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣ በድርጅቱ አማካይነትት በወቅቱ መተላለፋቸውን ይከታተላል።

3ድርጅቱ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች የክልሉ ሕዝብ ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆነ ይገመግማል፣ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆንባቸውን መንገዶችም በየጊዜው እየፈተሸ

provided, however, that it may also render partially or wholly-free services, as the case may require;

11. Undertakes studies and implements some upon presentation to and approval by the regional state proposals regarding the expansion of press, radio and television services equipped with appropriate technology in the region so that such services become efficient and qualitative in their provisions to the public;
12. Establishes working relation ships, in accordance with the country 's lows along with the domestic and external similar a agencies with the view to enhancing news reports and information exchange as well as benefiting from the necessary training and experience sharing in the field thereof;
13. Looks for and gathers any form of support from domestic and external agencies willing to provide material and financial support in accordance with the regional and national polices and laws;
14. Owns property, its name; enters into contracts, sues or be sued in its own name;
15. Carries out such other functions as may be necessary to accomplish its objectives.

Part Three
The Agency's Board Of Management And The Manager

8. Structure And Accountability Of The Board

1. The Agency shall be managed by the managing board to be constituted out of a membership not less than seven but not exceeding nine in number;
2. The members of the board shall be selected and appointed by the regional executive committee, out of the appropriate governmental bodies and sections of the society.
3. The board shall be accountable to the executive committee, of the regional state;
4. The chairperson of the board shall be selected and designated from among its members by the executive committee of the regional state.

The manager of the agency shall serve as the secretary of the board.

6. The board may, whenever it holds its sessions, have an assistant minute's person assigned with no vote by selecting one out of work divisions closely related to the task required.

9. Powers And Duties Of The Board

The board shall have the following powers and duties pursuant to this proclamation;

1. Ascertains that the agency implements lows, regulations and directives concerning mass media through out the region;
2. Follows that up the governmental policies, lows, regulations and directives of primary interest to the public are conveyed and brought to the attention of the people through the medium of the agency;
3. Evaluate to what extent that the people of the region have been benefiting from the services rendered by the agency and submits recommendations to the government after periodic

ለመንግሥት ሃሣብ ያቀርባል።

4.በዚህ አዋጅ መሠረት የሚፈጽማቸውን ተግባራት በተመለከተ ከሕዝብ በሚነሱ ስሞታዎችና በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ድርጅቱ ተገቢ ማብራሪያዎችን እንዲሰጥ ያደርጋል እንደአስፈላጊነቱም ስሞታዎችንና ቅሬታዎችን መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ ይሰጣል።

5.ድርጅቱ በብሔር ብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሃይማኖት እና በፖለቲካ አመለካከቶች መካከል ልዩነት ሣያደርግ ለሁሉም ወገኖች ሚዛናዊ የመረጃ ሽፋን መስጠቱን ይቆጣጠራል።

6.በክልሉ የመገናኛ ብዙሃን ተጀማች የሚሠራጩትን የዜና፣ የፕሮግራም እና የጋዜጣ ዘገባዎች አጠቃላይ ይዘት ይዝመግማል፣ ሰለሚሻሻሉበትም መንገድ ሃሳብ ያቀርባል።

7.የድርጅቱን ጋዜጠኞችና የቴክኒክ ባለሙያዎች ቅጥር፣ የደመወዝ ስኬልና ጥቅማጥቅሞች የአስተዳደርና የፋይናንስ መመሪያዎችን በማውጣት በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲፀድቁለት በሥራ ላይ ይውላል

8.የድርጅቱን መዋቅር ዝግጣም ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስፀድቃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

9.የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድ እንደዚሁም አመታዊ የካፒታልና የመደበኛ በጀት ተዘጋጅቶ እንዲቀረብ ያደርጋል፣ ይገመገማል፣ በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያሰፀድቃል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

10.ድርጅቱ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሳል።

11.ድርጅቱን በሚመለከቱ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሃሳብ ያቀርባል።

12. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ያወጣል።

10 የቦርዱ ስብሰባዎች

1. ቦርዱ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሄዳል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም በቦርዱ ሰብሳቢ ጥሪ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል አንድ ሦስተኛው ከጠየቁ በማናቸውም ጊዜ ለመሰብሰብ ይችላል።

3. በስብሰባው ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምላእተ ጉባዔ ይሆናል

4. ቦርዱ ማናቸውንም ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ሲሆን ድምፁ እኩል ለእኩል የሆነ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል።

5. ቦረዱ ይህንን አዋጅ ተከትሎ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. ሰለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

1. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተመርጦ የሚሾም ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ቦርዱና ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።

2 ሥራ አስኪያጁ በዚህ አንቀጽ 7 ላይ ለድርጅቱ

assessment of its prior activities to see to it that better and improved mechanisms of providing services are put in place;

4. calls on the agency to give appropriate explanations to public grievances and complaints arising from the nature of its duties performed in accordance with this proclamation examines and passes its own decisions as may be necessary;

5. Controls that the agency does provide all sides with afair and balanced opportunity of information coverage without necessarily discriminating any of them on the basis of their nation-nationality, sex, religion and political views and opinions

6. Reviews and evaluates the over all content of the news programs, as well as news paper reports disseminated through the regional mass media and there by submits recommendation to bring about their improvements;

7. Issues administrative and financial guidelines ones governing the employment, salary scale and fringe benefits of the agency 's Journalists and other technical employees and implements same upon submission to and approval by the regional executive committee;

8. Reviews the structure of the agency submits same to the regional executive committee and implements it upon approval thereof.

9. Makes sure that the agency's short, medium and long term plan as well as its annual capital and recurrent budget is prepared, submitted to and approval by the regional executive committee, after which it also follows up and supervisors over its implementation thereof';

10. Devises ways and mechanisms towards the strengthening of the agency and the improvement of its working procedures;

11. Undertakes consolations on and forwards considered opinions with regard to other policy issues concerning the agency;.

12. Formulates and issues various directives and guidelines which would facilitate the smooth implementation;

10. **Meetings Of The Board**

1. The board shall meet at least once in three months

2. With out prejudice to the provisions of sub-article (1) of this article hereof', the board may hold a meeting at any time whenever either the chairperson or one third of the members require it to do so in case of emergency;

3. There shall be a quorum where more than half of the members of the board are present at its meeting;

4. Any decision of the board shall be passed by a majority vote in case of a tie, however , the chairperson shall have a casting vote;

5. The board may issue its own rules of meeting procedures pursuant to this proclamation.

11. **Powers And Duties Of The Manager**

1. The manger of the agency shall be appointed by the regional executive committee and be accountable both to the said executive committee as well as the board of management respectively;

2. The manager shall, having been primarily entrusted with

በተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነቶች የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ. የድርጅቱን የዕለት ከዕለት ሥራዎች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል

ለ. የድርጅቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፣በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9/7/ ሥር በሚወጣው መመሪያ መሠረት ጋዜጠኞችንና የቴክኒክ ባለሙያዎችን ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣በሌላ በኩልም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በሲቪል ሠርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል::

ሐ. የድርጅቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ሲወሰንለት ተግባራዊ ያደርጋል::

መ. ለድርጅቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል::

ሠ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል::

ቀ. በድርጅቱ ውስጥ በሹመት ለሚያዙ የሥራ መደቦች እጩ ተሿሚዎችን በቦርዱ አማክኝነት ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል::

ረ. የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ወቅታዊ ዘገባዎችን ለቦርዱ እና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል::

ሸ. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

3. ሥራ አስኪያጁ ለድርጅቱ ሥራ ቅልጥፍና በአስፈላጊ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለቢታች የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::ሆኖም እርሱን ተክቶ እንዲሠራ ሥራ አስኪያጁ የሚወክለው ማናቸውም ሰው ከ30 ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለቦርዱ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል::

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. የድርጅቱ የበጀት ምንጭና አስተዳደር

1 የድርጅቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል::

ሀ.በክልሉ መንግሥት እንደአስፈላጊነቱ ከሚመደብለት የድጋፍ በጀት

ለ በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ

ሐ. ከሌሎች ምንጮች

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከሠ አስከ ሐ የተዘረዘሩት ምንጮች የሚገኘው ገቢ በድርጅቱ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ሆኖ የድርጅቱን ሥራዎች ለማከናወን በየጊዜው ወጭ ይደርጋል::

3. የድርጅቱ የገቢ አስተዳደርና አጠቃቀም ቦርዱ ወደፊት በሚያወጣውና የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሚያፀድቀው መመሪያ ይወሰናል::

13. የሂሣብ መዛግብት

1 ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችን ይይዛል::

2. የድርጅቱ ሂሣብ በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም በወጭ

discharging, up the foregoing powers and responsibilities of the agency indicated under article 7 of this proclamation hereof; have the following specific powers and duties;

a). Directs and supervises over the day-to day activities of the agency;

b). Organizes the office of the agency; employees and administers journalists and technical staff in accordance with the guideline to be issued pursuant to article 9(7) of this proclamation, provided, however, that he also employs and administers other support stuff in accordance with the civil service lows;

c). Prepares and submits to the board, draft working programme and budget proposal of the agency and implements same upon approval.

d). Effects expenditure in accordance with the approved annual budget and work programme of the agency;

e). Represents the agency in all its dealings with third parties;

f). Nominates and presents, to the regional executive committee through the agency of the board candidate appointees who are to occupy the distinct vacancies in the agency

g). Submits, to the board and the regional executive committee, periodic reports with regard to the activities of the agency;

h). Performs such other duties as may be referred to it by the board.

3. The manager may delegate part of his powers and duties to the subordinate officials and other employees of the agency to the extent necessary for the efficient performance of the activities of same; however, in the case of an official or employee who acts on be half of the manager for more than thirty days, the prior approval of the board shall be required

PART FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

12. **Budgetary Source And Administration**

1. The budget of the agency shall be drawn from the following sources:

a). Support budget which may be appropriated by the regional government for the agency, as necessary;

b). Service fees and charges collected by the agency pursuant to this proclamation;

c). Other unspecified sources.

2. All the revenues drawn from the sources specified from A-C of sub art (1) of this article hereof. shall be deposited in a bank account opened in the name of the agency to be expended for the under taking of the agency's activities

2. The agency's in come administration and utilization shall be determined by a directive to be issued by the board and approved by the regional executive committee.

13. **Books Of Account**

1. The agency shall maintain complete and accurate books of account and related documents.

3. The agency's account shall be audited by the regional auditor

አዲተሮች በየበጀት ዓመቱ ይመረመራል::

14 ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

11 የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1988 ዓ.ም አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 ና 4 ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል::

2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ሚሸፕ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

16 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባሕር ዳር
መጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ /ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

general or external auditors every fiscal year.

14. Power To Issue Regulations

The regional executive committee may issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.

15. Repealed And Inapplicable Laws

1. The provisions of sub-arts 1,2 and 4 of article 17 of proclamation No 4/1995 providing for the establishment of the Amhara National Regional state executive organs and the determination of their respective powers and duties are hereby repealed by this proclamation.
2. Any low, regulation, directive or common practice inconsistent with this proclamation shall be inapplicable to matters covered in this proclamation

16. EFFECTIVE DATE

This proclamation shall enter in to force as of the 27th day of March/2001.

Done at Bihar Dar
This 27th day of March 2001
Council of the Amhara National Regional State